DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

ታኅሣሥ (December) 20, 2016

ውድ የዲሲፒኤስ ተማሪዎች ወላጆች፣

የክረምቱን ወራት (winter) እየተቃረብን ስንመጣ ለአስከፊ አየር ንበረት መዘጋጀት ጀምረናል። በየዓመቱ ዋሽንግተን ለጥቂት ቀናት ትምህርት ቤቶችን የሚያዘጋ ወይንም በጣም ዘግይተው እንዲከፈቱ የሚያደርግ፣ ለጥቂት ቀናት በጣም ቀዝቃዛ ወይንም በረዷማ አየር ንበረት ያጋጥማታል። መጠንኛ የሆነ የክረምት ሁኔታ ያጋጥማታል ብለን ተስፋ የምናደርግ ሲሆን፣ ነገር ግን ይህ የማይሆን ሆኖ ከተገኘ ዝግጁ ሆነው እንዲገኙ እንፈልጋለን።

**ትምህርት ቤት እንዲዘጋ የምንወስነው እንዴት ነው?**
ትምህርት ቤቶች ዘግይተው እንዲከፈቱም ሆነ፣ እንዲዘጉ የሚደረገው በበርካታ ሁኔታዎች ላይ በመንተራስ በሚደረግ ውሳኔ ሲሆን፣ እነዚህም የአየር ንብረት፣ የነፋስ መቀዝቀዝ፣ የበረዶ እና የግግር በረዶ ሁኔታ መጠን፣ የመንገዶች ሁኔታ፣ የሕዝብ መጓጓዣዎች እና መመላለሻዎች መገኘት እና እነዚህም ሁኔታዎች በቀን ውስጥ ምን ያህል እየተከማቹ እንደሚሄዱ የሚደረጉ ትንበያዎችን ያካትታሉ። ከንቲባዋ፣ ከአየር ንበረት ኃላፊዎች እና ከከተማይቱ አስተዳደር ጠበብት ባለሙያዎች ምክሮችን በመቀበል በመጨረሻ ትምህርት ቤቶች ክፍት ሆነው እንዲቆዩ፣ ዘግይተው እንዲከፈቱ፣ ወይንም እንዲዘጉ በመጨረሻ ይወስናሉ። አብዛኛውን ጊዜ ውሳኔው ከ 4:00-5:00 ኤኤም ድረስ ባለው በዚያኑ ትምህርት ቤቶች ዘግይተው በሚከፈቱበት ወይንም ዝግ ሆነው በሚውሉበት ማለዳ ላይ ይወሰናል።

**ሕዝቡ ስለ ትምህርት ቤቶች መዘጋት እንዲያውቅ የሚደረገው እንዴት ነው?**
እጅግ በጣም ጥሩ መረጃ የሆነው የዲሲፒኤስ ቲዊተር አካውንት (DCPS Twitter account) የሆነው (@dcpublicschools) ነው። መረጃዎች በተጨማሪ የዲሲፒኤስ ድረ ገጽ በሆነው (dcps.dc.gov)፣ በዲሲፒኤስ ማኅበራዊ የብዙኃን መገናኛ አካውንትስ (DCPS social media accounts) እና በክልል የቴሌቪዥን እና የሬዲዮ ጣቢያዎች አማካይነት እንዲገለጽ ይደረጋል።

**2-ሰዓት ዘግይቶ መከፈት ማለት ምን ማለት ነው?**
መዘግየት፣ ትምህርት ቤቶች ከመደበኛው ትምህርት መጀመሪያ ጊዜያት 2 ሰዓት ቆይተው እንዲከፈቱ የሚያደርግ ነው። ዘግይቶ መከፈት "እንደ በረዶ ቀን" ("snow day") የማይቆጠር ሲሆን፣ በትምህርት ዓመቱ ውስጥም በኋላ ሊካካስ የሚገባው አይደለም። በተጨማሪም ማናቸውም ከትምህርት ሰዓት በፊት የሚካሄዱ ፕሮግራሞች እንዲሰረዙ ነው የሚደረገው። ትምህርት ቤቶች የደወል ሰዓቶቻቸውን ጊዜያቶች በየግላቸው እንደ አመቻቸው በመዘግየቱ ምክንያት ቁርስም ያስተናግዱ እንደሆነ ያመቻቻሉ። በአየር ንበረት መዛባት ምክንያት የተነሣ የትምህርት ቤት መከፈት የሚዘገይ ከሆነ፣ የከትምህርት በኋላ ፕሮግራሞች እንደበፊቱ በተያዘላቸው ጊዜ ሥራቸውን ያከናውናሉ።

**በትምህርት ቀን አስከፊ የአየር ንብረት ሁኔታ ቢፈጠርስ?**
ከትምህርት ቤት ወደ ቤትና ከቤትም ወደ ትምህርት ቤት መመላለስ የተማሪዎችን የድህንነት ሁኔታ የሚፈታተን ሆኖ በሚገኝበት እና ይህንን የመሳሰሉ ሁኔታዎች በሚፈጠሩበት ጊዜ ቀደም ብሎ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ሊለቁ ይችላሉ። ቻንስለሩ፣ የተራዘሙ የትምህርት ፕሮግራሞች፣ ከትምህርት በኋላ ፕሮግራሞች፣ ወይንም የስፖርት ክንውኖች፣ ወይንም የአቴሊአቲክ ክንውኖችን ለመሰረዝ ይወስናሉ። ትምህርት ቤቶችን ቀደም ብሎ ለመዝጋት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ዲሲፒኤስ ወዲያውኑ ለትምህርት ቤቶችና ለወላጆች ስለ መዘጋቱ ያስታውቅ እና ተማሪዎችም በሙሉ ከመለቀቃቸው በፊት ምሳ እንዲመገቡ ይደረጋል። የትምህርት ቤቶች መከፈት በአየር ንበረት መዛባት ምክንያት የዘገየ ከሆነ፣ ከትምህርት በኋላ ፕሮግራሞች በተያዘላቸው ጊዜ መሠረት እንዲካሄዱ ይደረጋል።

**የባከኑ የትምህርት ቀናት መቼ ነው እንዲካካሱ የሚደረገው?**
የዲሲስቴት ሕግ (State law)፣ ዲሲፒኤስ 180 የትምህርት ቀናት እንዲኖሩት ይጠይቃል። እነዚህን ሊሟሉ የሚጠበቁ የተለመዱ የትምህርት ቤቶች ቀናትን ለማሟላት በዓመቱ ትምህርት ማብቂያ ወቅት ላይ ጥቂት ቀናት እንዲካካሱ ይደረጋል።

- **1 የበረዶ ቀን (1 snow day)**፣ ከገጠመን በትምህርት ቤቶች የትምህርት ቀናት መቁጠሪያ ላይ አንዳችም ለውጥ አይኖርም።
- **2 የበረዶ ቀናት (2 snow days)**፣ ከገጠመን፣ ሰኔ (June) 14 ሙሉ የትምህርት ቀን ሆኖ የሚውል ሲሆን፣ ሰኔ (June) 15 ግማሽ የትምህርት ቀን ሆኖ በማገልገል ተማሪዎች በ 12:15 ፒኤም ላይ እንዲለቀቁ ይደረጋል።
- **3 የበረዶ ቀናት (3 snow days)**፣ ከገጠመን፣ ሰኔ (June) 14 እና 15 ሙሉ የትምህርት ቀናት ሆነው የሚውሉ ሲሆን፣ ሰኔ (June) 16፣ ግማሽ የትምህርት ቀን በመሆን በ 12:15 ፒኤም ላይ ተማሪዎች ይለቀቃሉ።

የተራዘመ የትምህርት ዓመት (Extended Year schools) ትምህርት ቤቶች ሊሟሉ የሚገባቸውን 180-የትምህርት ቀናት በልጠው የሚገኙ ሲሆን፣ የበረዶ ማካካሻ ቀናት አይኖራቸውም።

ከልባዊ ሠላምታ ጋር፣

Jane Spence
ጊዜያዊ የትምህርት ቤቶች ዋና ሥራ አስኪያጅ (Interim Chief of Schools)